ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU
MIDDLE LEVEL SCHOOL (GRADE 8) LEAVING CERTIFICATE
EXAMINATIONS *SENE 2017E.C/JUNE* 2025G.C

GENERAL DIRECTIONS

THIS BOOKLET CONTAINS TWO EXAMINATIONS: **AMHARIC AND ENGLISH**. EACH EXAMINATION IS TO BE DONE ON A SEPARATE ANSWER SHEET. THE TIME ALLOWED FOR EACH EXAMINATION IS EXACTLY 1 HOUR.

THE FIRST PART IS AMHARIC (first language) EXAMINATION, WHICH CONTAINS 60 ITEMS AND THE SECOND PART IS ENGLISH EXAMINATION, WHICH ALSO CONTAINS 60 ITEMS.

EACH QUESTION HAS FOUR CHOICES MARKED A, B, C, AND D. READ EACH QUESTION AND THE CHOICES CAREFULLY. THEN MARK YOUR CHOICE ON THE SEPARATE ANSWER SHEET YOU ARE PROVIDED.

USE ONLY PENCIL TO MARK YOUR ANSWERS. YOUR ANSWER MARK SHOULD BE HEAVY AND DARK THAT COVERS THE SPACE COMPLETELY. PLEASE ERASE ALL UNNECESSARY PENCIL MARKS COMPLETELY FROM YOUR ANSWER SHEET. IF YOU CHOOSE ALTERNATIVE "C", FOR EXAMPLE, MARK THE THIRD SPACE LIKE THE FOLLOWING:

| A | B | C | D |
|---|---|---|---|
| ○ | ○ | ● | ○ |

IF YOU FINISH BEFORE TIME IS CALLED, YOU MAY GO BACK AND REVIEW YOUR WORK. WHEN TIME IS CALLED, YOU MUST IMMEDIATELY STOP WORKING, LAY YOUR PENCIL DOWN, AND WAIT FOR FURTHER INSTRUCTIONS.

ANY FORM OF CHEATING OR AN ATTEMPT TO CHEAT IN THE EXAMINATION WILL RESULT IN AN AUTOMATIC DISMISSAL FROM THE EXAMINATION HALL AND CANCELLATION OF YOUR SCORE(S).

**DO NOT TURN THIS PAGE UNTIL YOU ARE TOLD TO DO SO!**

LIVEWORKSHEETS

**መመሪያ አንድ፡ ከዚህ ቀጥሎ አራት አራት አማራጭ መልሶች ያላቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በመልስ መስጫው ላይ በማጥቆር መልስ/ሺ።**

1. በማህበራዊ ግንኙነት ሂደት አንድ ተናጋሪ ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን እንዲተገበር ይጠበቃል።
   A. አዋቂዎችን እንደ ህጻናት ማናገር
   B. ከወንዶች ይልቅ ሴቶችን ማክበር
   C. የንግግር ተሳታፊዎችን ማክበር
   D. ህጻናትን ገለጥ አድርጎ መያዝ
2. ንግግር ................ነው።
   A. ሰዎች እንደረዱት አድርጎ ሀሳብን በቃል የመግለጽ ችሎታ
   B. መልእክት ተቀባይ በጽሑፍ አማካኝነት መረጃ የሚያገኝበት
   C. በቴሌቪዥን የሚተላለፍን መልእክት በቀላሉ የምንገነዘብበት
   D. በስብሰባ ላይ የሚደረግ ውይይት ተዘግቦ ሰነድ የሚደረግበት
3. ከሚከተሉት አንዱ ትክክለኛ የሆነ የንግግር ስርአት ተከናውኖበታል።
   A. በዛሬው ውይይት ላይ ሀሳብ ሳቀርብ ድንብርብሬ ወጣ።
   B. በውይይቱ ላይ ያቀረብከው ሀሳብ ዝብርቅርቅ ያለ ነው።
   C. በዛሬው ውይይት ላይ ከፍተኛ የሆነ የመረጃ እጥረት ገጠመኝ።
   D. በየትኛውም ውይይት ላይ ስሳተፍ ተራዬን ጠብቄ እናገራለሁ።
4. ሰዎች እንደ ማህበረሰብ እርስ በእርስ የሚያደርጉት ግንኙነት ለምን ያገለግላል?
   A. አንዱ በሌላው መጎዳት እንዲስቅ
   B. እርስ በእርስ መደጋገፍ እንዲችሉ
   C. አንዱ ሌላውን አሸንፎ እንዲጥለው
   D. አንዱ በሌላው ላይ ጥገኛ እንዲሆን



LIVEWORKSHEETS

## አማርኛ ፈተና 8ኛ ክፍል 2017 ዓ.ም

5. የንግግር አቀራረብ መርህ ተግባራዊ የተደረገበት ከሚከተሉት ውስጥ የቱ ነው?
   A. "ዛሬ በንግግር የማቀርብላችሁ ሀሳብ 'ንብ ሁኑ' በሚል ርእስ ላይ ያጠነጥናል::"
   B. "አድማጮች ከየቦታው ተሰባስባችሁ መምጣታችሁ ትንሽ አስጨንቆኛል::"
   C. "ጀለሶቹ ብዙ ዝግጅት ባይኖረኝም ከማውቀው በመነሳት ከብዙ ጥቂት ልበል::"
   D. "ያቀረብኩትን ሀሳብ በደንብ ስለምታውቁት አስተያየት እንድትሰጡኝ አልፈልግም::"

6. "መምህራችን ምግብ በልተን የአካል እንቅስቃሴ ካላደረግን ክብደታችን እንደሚጨምር ነገሩን::" በሚለው ንግግር ውስጥ ---------- አለው::
   A. በአሳማኝ ምክንያት ያልተደገፈ ሀሳብ
   B. ለተሳሳተ ድምዳሜ የሚዳርግ መረጃ
   C. በእስፖርተኞች የሚተረክ አፈ ታሪክ
   D. ጥሩ የምክንያትና የውጤት ግንኙነት

7. ከሚከተሉት ውስጥ ,አንዱን ተግባራዊ ማድረግ በክርክር ሂደት ውጤታማ ያደርጋል::
   A. ተቃራኒ ቡድንን በሀሳብ መደገፍ
   B. ሀሳብን በምክንያት ማስደገፍ
   C. የሌላውን ቡድን ሀሳብ መቀበል
   D. የተልፈሰፈሰ ምክንያት ማቅረብ

8. ከሚከተሉት ንግግሮች ውስጥ አንዱ የምክንያትና ውጤት ትስስር አለው::
   A. "ሰውየው በጣም እየተጣደፈ ወደ ስራ ሄደ::"
   B. "ትምህርት ቤት የእውቀት መገብያ ነች::"
   C. "ጁሙን ሲያሳድገው ጊዜ ሌላ ሰው መሰለ::"
   D. "ዛሬ በህልሜ ረዥም ሩጫ ስሮጥ አየሁ::"

9. ከሚከተሉት ቃላት መካከል ተዘውትሮ በጥቅም ላይ የሚውለው ……… ነው::
   A. አንጎለ
   B. አበቀ
   C. አበተ
   D. አጉዘለ



LIVEWORKSHEETS

# አማርኛ ፈተና 8ኛ ክፍል 2017 ዓ.ም"

10. "አባቷ ግርማ ሞገስ ያለው ሰው መሆኑን ተመልክታ ......!!" ይህንን አረፍተ ነገር የተሟላ የሚያደርገው ቃል የቱ ነው?

A. ታመመች

B. ተስቀለች

C. ተዘቀዘቀች

D. ተደመመች

11." አንተ ልጅ! ከዚች ደቂቃ ጀምሮ .........." የሚለውን አረፍተ ነገር የተሟላ ሊያደርገው የሚችለው የቱ ነው?

A. እናቱን እወዳት ነበር::

B. ጣቱን አሞኝ ነበር!

C. እጅህን ከላዩ አንሳ!

D. ወንድሜን አየኸው?

12. "በመንገዱ ዳርና ዳር የተተከሉት አምፖሎች ብርሃን <u>ይተፉሉ</u>::" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ......... የሚል ፍቺ አለው::

A. አስመለሰ

B. አመነጨ

C. አንጸባረቀ

D. አጥበረበረ

13. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ጥምር ቃል ነው::

A. የወተት እቃ

B. የጡት ልጅ

C. ጥሩ ወርቅ

D. ሆደ ሰፊ

14. "ልጅቷ በወንድሟ ስርግ ላይ ጭፈራውን <u>አስነካችው</u>::" የሚለው አረፍተ ነገር ልጅቷ ......... ይገልጻል::

A. በደንብ መጨፈሯን

B. ለታይታ መንቀሳቀሷን

C. ከጭፈራ መከልከሏን

D. ለወጉ መወዛወዟን

15. "ቤቱ ሙሉ መሆኑን አይቼ ለአናጺው ወንድሜ ጥሩ <u>ቀፍቃፊ</u> መሆኑን ነገርኩት::" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ለተሰመረበት ቃል ፍካሬያዊ ፍቺ የሚሆነው የቱ ነው?

A. ረባሽ

B. ባለሙያ

C. ወላድ

D. አንጥረኛ

16. "<u>ቁርጥ</u> መሆኑ ከታወቀ ለምን እንዘገያለን? ምሳችንን እንብላና ጉዟችንን እንጀምር::" በሚለው ንግግር ውስጥ ለተሰመረበት ቃል እማሬያዊ ፍቺው ............ ነው::

A. የተለየ

B. እርግጠኛ

C. ሙዳ ስጋ

D. ሆድ አባቢ



LIVEWORKSHEETS

17. "በተከሰተው የጉሮ ውድነት አሮሮ ያላሰማ ሰው የለም።" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ለተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ የሚሆነው የቱ ነው?

A. ሀዘን

B. ጩኸት

C. ኡኡታ

D. ምሬት

18. "እህቱ ያስበችውን እሳከታ በማየቱ አፎይታ ተሰምቶኛል።" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ ...... ነው።

A. እረፍት

B. ድካም

C. ጭንቀት

D. ሰላም

19. "የተቸገሩ ሰዎችን አይተው ማለፍ የማይችሉ ብዙ ሩህሩህ ሰዎችን አይቻለሁ።" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ተቃራኒ ....... ነው።

A. የዋህ

B. አልቃሽ

C. ጨካኝ

D. ጥዩፍ

20. "የበኩር ልጁ እድጎ እድጎ ቁልቁል ያየኝ ጀመር።" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ለተሰመረበት ቃል ተቃራኒ የሚሆነው የቱ ነው?

A. ታች

B. ሽቅብ

C. በላይ

D. ንቀት

**መመሪያ ሁለት:- ምንባብ አንድን በጥንቃቄ ካነበባችሁ በኋላ ከተራ ቁጥር 21-26 ለቀረቡት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጭ መልሶች መካከል ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በመልስ መስጫው ላይ አጥቁር/ሪ።**

በማህበረሰብ አኗኗር ሂደት ግጭት ቢከሰትም የፍቅርና የሰላም መሰረት በሆነው በእርቅ ይፈታል። ግጭት በተዳር አጋሮች፣ በቤተሰብ አባላት ወይም የማህበረሰብ ክፍሎች መካከል ሊከሰት ይችላል። በተግባቦት ሂደት የሚፈጠር አለመግባባት፤ የተሳሳተ ግንዛቤ፤ የመረጃ ክፍተት፣ ስህተት፣ እጥረትና መዛባት፤ የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት፤ ኢፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል እንዲሁም በስሜታዊነት የሚከናወኑ ተግባራት መንስኤዎቹ ሊሆኑ ይችላሉ።



LIVEWORKSHEETS

እርቅ ግጭቱ ያስከተለውን ችግር ለመፍታት ያስችላል። አፈታቱ ውጤታማ እንዲሆን መንስኤ በሆኑት ጉዳዮች ላይ በደንብ ተወያይቶ መግባባት፣ መደማመጥ፣ የሌሎችን እይታ መረዳትና መቻቻል ያስፈልጋል። እርቁ ጠቡ ባስከተለው ጥላቻና መፈራራት ምክንያት ተራርቀው የነበሩ ሰዎች የፈረሰውን የጋራ ኑሯቸውን መልሰው እንዲገነቡ ያስችላቸዋል። በእርቁ ሂደት የሚኖረው የውሳኔ አሰጣጥ እንደ መደበኛ ፍርድ ቤት አንዱ ሲፈረድለት ሌላው የሚፈረድበት አይደለም። ይልቁንም እንደ አስፈላጊነቱ በዳዩ እንዲክስና ሁለቱም አሸናፊ የሚሆኑበት ነው። ይህ ደግሞ አብሮነታቸውን፣ አንድነታቸውንና ፍቅራቸውንም ወደ ነበረበት ይመልሳል።

ያለዕርቅ ሰላም፣ ያለሰላም የመኖር ህልውና ሊኖር አይችልም። ስለዚህም ማህረሰቡ እርቅን ተግባራዊ ቢያደርግ ተጠቃሚ ይሆናል። የመኖር ህልውናው ተረጋግጦ በተረጋጋ ሁኔታ ለመኖር ያስችለዋል። እናም የትኛውም ጥላቻ ሲከሰት አመርቅዞ በቀልን ከመውለዱ በፊት በእርቅ ሊፈወስ ይገባል። ፈውሱ ፍቅርን፣ አንድነትን፣ መተሳሰብንና መከባበርን ለማስፈን ያስችላል።

ከማለዳ ማርቆስ። 2012። የኮሬ ማህበረሰብ የእርቅ ስነስርአት (ያልታመ) ተሸሽሎ የተወሰደ።

21. ከሚከተሉት ውስጥ ለዚህ ምንባብ ተስማሚ የሚሆነው ርእስ የቱ ነው?

A. የግጭት መነሻ

B. ጠብን መፈወስ

C. የሰላም ጥሪዎች

D. ግጭትና እርቅ

22. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የሁለተኛው አንቀጽ ሀይለ ቃል ነው።

A. እርቅ ግጭቱ ያስከተለውን ችግር ለመፍታት ያስችላል።

B. በእርቁ ሂደት ከሳሽም ተከሳሽም አሸናፊዎች ይሆናሉ።

C. በጠብ ምክንያት ተራርቀው የነበሩ ሰዎች ይቀራረባሉ።

D. ታራቂዎቹ አንድነታቸውንና ፍቅራቸውን ያድሱታል።



LIVEWORKSHEETS

23. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የምንባቡን መሰረተ ሀሳብ ይገልጻል።
   A. ግጭትን በእርቅ የሚፈቱ ፈሪዎች ናቸው።
   B. ማህበረሰብ እርስ በእርስ ሊጋጭ አይችልም።
   C. እርቅ ሰላማዊ የግጭት መፍቻ መንገድ ነው።
   D. ግጭት እርስ በእርስ ለመፈታተሽ ያስችለናል።

24. በምንባቡ ውስጥ "አመርቅዞ" የሚለው ቃል ........... የሚል አውዳዊ ፍቺ አለው።
   A. አመመ
   B. ተባባሰ
   C. ጠዘጠዘ
   D. አገረሸ

25. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ በምንባቡ ውስጥ መፍትሄ ሆኖ የቀረበ ነው።
   A. አለመግባባት
   B. የሀሳብ ልዩነት
   C. የሀብት ክፍፍል
   D. ሌሎችን መረዳት

26. በምንባቡ መሰረት ............ ከ........... ይቀድማል።
   A. ጥላቻ ከበቀል
   B. እርቅ ከግጭት
   C. ግጭት ከልዩነት
   D. መቻቻል ከግጭት

**መመሪያ ሶስት:- ምንባብ ሁለትን በጥንቃቄ ካነበባችሁ በኋላ ከተራ ቁጥር 27-36 ለቀረቡት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጭ መልሶች መካከል ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በመልስ መስጫው ላይ አጥቁር/ሪ።**

## ምንባብ ሁለት

መልአከ ሞት በድንገት ሹልክ ብሎ ኮሽታ ሳያሰማ ከመኝታ ቤቴ ዘልቆ ገባ። ከዚያም "ነገ ልወስድህ ነውና ተዘጋጅ" አለኝ። ይህ ስራ ፈት! እጅግ የሚያበሳጭ ትእዛዝ ነው። አልሄድም!

በምድር ላይ እጅግ ብዙ ነገሮችን ለመስራት አቅጃለሁ። በርካታ ጥበቦች በልቤ ጢም ብለው ሞልተው ሊፈሱ ነው። ደግሞም ከልጅነቴ ጀምሮ ከአፈር ጋር የተዋሀደው ደሜ ምድርን እንዲህ በዋዛ ተሰናብቶ አይሄድም። ጥፍጥ ብሎ የቀረበልኝን የህይወት ማእድ ጥሎ እብስ



LIVEWORKSHEETS

# 1 አማርኛ ፈተና 8ኛ ክፍል 2017 ዓ.ም

ለማለት የበረታ ልብ የለኝም። ጊዜዬ ገና ነው። እስቲ የተወለዱት ልጆቼ ይደጉ፤ የተረገዘውም ይወለድና በምድር ላይ ሲመላለስ ልየው። ባልጠነከሩ እግሮቹ በርትቶ ለመቆም ሲውተረተር ልመልከተው። ያልተከላትን አበባ ሲቀጥፍ፣ ብርጭቆ ሲሰብርና የጎረቤት ልጅ አስለቅሶ ሲመጣ ልቆጣው። ጆሮዬ ጥዑም ሙዚቃና የደሬድ ዝማሬ እንጂ በፍጹም የእሱን "የሞት ጥሪ" አይሰማም። ጊዜ አልተረፈኝም፤ ገና እንዲያውም አልበቃኝም። እኔ እንደሚታረድ በግ አንገቴን ደፍቼ የምከተለው መስሎሃል። ከእሱ ጋ ስንከራፈፍ ረብጣ፣ ረብጣ የህይወት ትሩፋቶቼን አላባክንም።

ገና ዓይኔን በምድር ላይ አመላልሼ መስኮቼን አያለሁ። ውቂያኖሶቿንና ተራሮቿን እጎበኛለሁ። አይኔን ከህዋው መንደር ልኬ በውበታቸውን እደመማለሁ። በጥልቅ የፍቅር ተመስጦ ወደ ሰማዩ ተንጥቄ ከዋክብቱ ባቀረቡልኝ የብርሃን ድግስ እታደማለሁ። የሀገሬ ባለቅኔ እንዳለው፦

"ማን ያውቃል?
አድናቂ ልቤና የምሽት ኮከቧ
ቀጠሮ እንዳላቸው ከፍቅር ወደቧ?"

ብዬ እቀኛለሁ። ገና ከፏፏቴው ስር ሆኜ ከሚወረወረው ውሀና በእርጋታ ከሚፈሰው ወንዝ ጋር የሆድ ሆዴን አወጋለሁ። ንፋሱን በእጆቼ እየዳበስኩ፣ በገላዬ እያቀፍኩ ምሽቱን አሳልፋለሁ። ጨረቃም በቅናት ድብን ትበል፣ ታልቅስ ከፈለገች! ስንት ትውልድ በትዕግስት እያሽኮረመመ የራሱ ሊያደርጋት ቢከጅልም እሷ እዚያ ላይ ተንጠልጥላ እምቢ አታገኙኝም ብላለች። እኔ የሩቅ ዘመድ አልፈልግም። ስለዚህ ወደ እርሷ አላማትርም።

የሞት መልአክ ኮሽታ ሳያሰማ ይኸው ከፊቴ ተገትሯል። እኔ ግን አልበረግግለትም፤ አልፈራውምም። የነገረኝንም አልቀበለውም። "ሞት ሆይ አትወስደኝም! አንተ የምታውቀው ያልፈጠርካትን ነብስ 'ልውሰድ' እያልክ መጋበዝን ብቻ ነው፤ ማጋዝ፤ ማጋዝ፤ ማጋዝ፤ እኔን አትወስደኝም።" ወደድከም ጠላህም እኔ ሞት በማይደርስበት፣ ፀሀይ በምትነግስበት፣ ነጻነት ሞልቶ በፈሰሰበት አለምገና ብዙ እኖራለሁ።" እለዋለሁ።

ከዓለማየሁ ንጌሴ። "እምቢ፣አልሞትም!፣በአዳም ረታና ሌሎች እውቅ ጸሐፍያን"፣ አማሌሌ። ገጽ 200-202። ተሻሽሎ የተወሰ



LIVEWORKSHEETS

27. በምንባቡ ውስጥ የሚናገረው ሰው መሞትን ........።
A. አይፈልግም
B. ይፈራል
C. ያደንቃል
D. አያከብርም

28. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የምንባቡ ርእስ ሊሆን ይችላል።
A. የከዋክብት ውበት
B. ልጆቼን ላሳድግ
C. እምቢ አልሞትም
D. እምቢ አታገኙኝም

29. የዚህ ምንባብ ሁለተኛ አንቀጽ ሀይለ ቃል ........ ነው።
A. በርካታ ጥበቦች በልቤ ጢም ብለው ሞልተው ሊፈሱ ነው።
B. በምድር ላይ ገና እጅግ ብዙ ነገሮችን ለመስራት አቅጃለሁ።
C. እኔ እንደሚታረድ በግ አንገቴን ደፍቼ የምከተለው መስሎታል።
D. እስቲ የተረገዘው ልጅ ይወለድና በምድር ላይ ሲመላለስ ልየው።

30. በዚህ ምንባብ አማካኝነት መግለጽ የተፈለገው ምንድነው?
A. የሚጋፈጠው ካገኘ ሞት ሰዎችን አይወስድም።
B. ተፈጥሮን ማድነቅ የሰው ልጅ ተፈጥሮው ነው።
C. ሞት ደካማ ደካማውን መርጦ መውሰድ አለበት
D. ሞት የሰዎችን ህልም የሚያሰናክል ጉዳይ ነው።

31. በምንባቡ ውስጥ "ማእድ" የሚለው ቃል አውዳዊ ፍቺ ......... ነው።
A. ገበታ
B. መዓዛ
C. ትሩፋት
D. መዐድን

32. በምንባቡ ውስጥ "እብስ አለ" የሚለው አገላለጽ ከ...... ጋር የተያያዘ ነው።
A. ፍጥነት
B. ስንብት
C. ማታለል
D. ዝግጅት

33. በምንባቡ ውስጥ "ማጋዝ፣ ማጋዝ፣ ማጋዝ" ተብሎ ተገልጿል። እንዲህ የሚጋዘው ምንድነው?
A. የሰው ልጅ
B. ሞት
C. እቃ
D. ጓዝ ጉዝጓዝ



LIVEWORKSHEETS

34. በምንባቡ ውስጥ የሚናገረው ሰው "...ፀሀይ በምትነግስበት፣ ነጻነት ሞልቶ በፈሰሰበት አለም ገና ብዙ እኖራለሁ..." ማለቱ ምን ያመለክታል?

A. ሰው ከሞት ጋር መታረቁን
B. ሞት ውሳኔውን መለወጡን
C. የሞትን ውሳኔ አለመቀበሉን
D. ተናጋሪው አቋሙን መቀየሩን

35. በምንባቡ ውስጥ የሚናገረው ሰው የምን አድናቂ ነው?

A. የቤተሰቡ
B. የህይወቱ
C. የጀግኖች
D. የተፈጥሮ

36. በምንባቡ ውስጥ የሚናገረው ሰው ምን አይነት ነው?

A. ተስፋ የቆረጠ
B. ለመስራት ያቀደ
C. ለግብግብ የተዘጋጀ
D. ህይወትን ያጣጣመ

**መመሪያ ፬: ቀጥሎ የቀረበውን ጽሑፍ መሰረት በማድረግ ከተራ ቁጥ 37-40 ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በመልስ መስጫው ላይ አጥቁር/ሪ::**

ዓለም በከፍተኛ የለውጥ ሂደት ላይ ትገኛለች:: በአሁኑ ወቅት በአለም ላይ በየሰኮንዱ በርካታ አዳዲስ ግኝቶች እየተከሰቱ ነው:: ሳይንስና ቴክኖሎጂ ወደ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ እየተሸጋገሩ ይገኛሉ:: ከዚህ ጋር ተያይዞ የሰው ልጅም በፈጣን ሁኔታ እየተቀየረ ነው:: የምርት አይነቶችም እንዲሁ ወደ ላቀ ደረጃ እየተሸጋገሩ ናቸው::

37. ይህ ጽሁፍ ........ ነው::

A. አዝናኝ
B. ቀስቃሽ
C. ኢመደበኛ
D. መደበኛ

38. የዚህ አንቀጽ ሀይለ ቃል የቱ ነው?

A. ዓለም በከፍተኛ የለውጥ ሂደት ላይ ትገኛለች::
B. ሳይንስና ቴክኖሎጂ ወደ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ እየተሸጋገሩ ይገኛሉ::
C. በአለም ላይ በየሰኮንዱ በርካታ አዳዲስ ግኝቶች እየተከሰቱ ነው::
D. ከዚህ ጋር ተያይዞ የሰው ልጅም በፈጣን ሁኔታ እየተቀየረ ይገኛል::



LIVEWORKSHEETS

39. በጽሑፉ ውስጥ "ከዚህ ጋር ተያይዞ የሰው ልጅም በፈጣን ሁኔታ እየተቀየረ ነው::" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት እንዴት ያሉ ሀሳቦችን ለማያያዝ አገልግሏል።

A. ተቃራኒ

B. የተዘረዘረ

C. ተጨማሪ

D. ተመሳሳይ

40. ይህ ጽሑፍ ከየትኛው የድርሰት አይነት ይመደባል?

A. ገላጭ

B. ስእላዊ

C. አዝናኝ

D. ተራኪ

41. "የዘንድሮ ምርት የተትረፈረፈ ከመሆኑም በላይ ጥራቱ ደረጃውን የጠበቀ ነው::" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት እንዴት ያሉ ሀሳቦችን ለማያያዝ አገልግሏል?

A. ተቃራኒ

B. ተጨማሪ

C. ተብራሪ

D. አብራሪ

**መመሪያ ፭: ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በመልስ መስጫው ላይ አጥቁር/ሪ::**

42. " እኔ ከታላላቆቼ ብዙ ተምሬያለሁ ....... አርአያዎቼ መሆናቸው የማይካድ እውነታ ነው::" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ያለውን ባዶ ቦታ የተሟላ የሚያደርገው ......... ነው::

A. !

B. ፣

C. ፤

D. ?

43. "በእግሬ ድክ ድክ ከምልበት ጊዜ አንስቶ በአባቴ እግር ስር ተቀምጬ ስነምግባር ተማርኩ። አሁን ተራው የእኔ ሆነና ልጆቼን እያስተማርኩ ነው::" የሚለው ጽሑፍ ....... ድርሰት ሊሆን ይችላል።

A. ስእላዊ

B. አመዛዛኝ

C. ገላጭ

D. ተራኪ



LIVEWORKSHEETS

44. "አስረስ ...... ከድርና ፍራኦል የትምህርት ቤታችን የእግር ኳስ ተጫዋቾች ናቸው::" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ባዶ ቦታውን የተሟላ የሚያደርገው ስርአተ ነጥብ የቱ ነው?

A. ፡

B. ፤

C. !

D. ?

45. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ በትክክል የተዋቀረ አረፍተ ነገር ነው::

A. እናትነት እጅግ በጣም ትልቅ ኃላፊነት ነው::

B. ህፃናትን መንከባከብ ድርሻ የወላጆች ነው::

C. ህፃናቶች ሲጣሉ እርስ በእርሳቸው ይችላሉ::

D. እኔ ቃላት እናትነትን ለመግለጽ ያጥሩኛል::

46. የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች በየትኛው ቅደም ተከተል ቢዋቀሩ የተስተካከለ አንቀጽ ይመሰርታሉ?

ሀ. ጉዳቱ በተፈጥሮ አደጋ፣ በድርቅና በርሃብ በቀላሉ መጠቃት ነው::

ለ. ሲጠቀም እነዚህን የተፈጥሮ ፀጋዎች በአግባቡ ካልተንከባከበ ለጉዳት ይዳረጋል::

ሐ. የሰው ልጅ ለመኖር መሬትን፣ ዕፅዋትን፣ እንስሳትንና፣ ውሃን ይጠቀማል:: :

መ. በነዚህ ችግሮች ሳይጠቃ ለብዙ አመታት ሳይቸገር እንዲጠቀምባቸው ሊንከባከባቸው ይገባል::

A. መ፣ ሐ፣ ሀ፣ ለ

B. ለ፣ መ፣ ሐ፣ ሀ

C. ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ መ

D. ሐ፣ ለ፣ ሀ፣ መ

47. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል አንዱ በአሁን የድርጊት መፈጸሚያ ጊዜ የተጻፈ ነው::

A. ጉርሜሳ ከትምህርት ቤት መጥቶ ተኛ::

B. ጌታቸው ከስራ ወደ ቤት እየሄደ ነው::

C. ወርቂቱ ገበያ ሄዳ ከመጣች ቆይታለች::

D. ወደርየለሽ ወደ ሀገሬ እሄዳለሁ ብላለች::



LIVEWORKSHEETS

48. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ውስብስብ አረፍተ ነገር ነው።

A. ጫልቱ የጡት እናቷን ትወዳቸዋለች።

B. ሰብስቤ ጠዋት ጠዋት ቤቱን ያጸዳል።

C. ወርቁ ልጇን ጡት አጥብታ አስተኛች።

D. ኡመር የስፈሩን አረጋውያን ይረዳል።

49. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል በኃላፊ ጊዜ የተጻፈው የቱ ነው?

A. በዚህ አመት ብዙ ምርት ተገኝቷል።

B. ፈተናውን ለማለፍ በርትቼ አጠናለሁ።

C. ግቢያችን ውስጥ አትክልት እተክላለሁ።

D. ለታላቁ ሩጫ በቂ ዝግጅት አደርጋለሁ።

50. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ አንዱ /-ኦች/ን በመቀጠል ወደ ብዙ ቁጥርነት ይቀየራል።

A. ሻማ

B. ገበሬ

C. ወንዝ

D. በሬ

51. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል አንዱ በወደ ፊት የድርጊት መፈጸሚያ ጊዜ የተጻፈ ነው።

A. ሰሜን ተራሮችን በደንብ ጎብኝቻለሁ።

B. ጥርሴን ከነቀልኩ ሰባት አመት ሆነኝ።

C. ልጁ ሲያለቃቅስ እንደነበር አይቻለሁ።

D. ሶፍኡመር ዋሻን ለመጎብኘት እሄዳለሁ።

52.ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ --------- /-ዎች/ን በመቀጠል ብዙ ቁጥርን ይገልጻል።

A. ልብስ

B. ጥሩንባ

C. ወዛደር

D. ዝነኛ

53. "ገብሬ ውሃ <u>በብርጭቆ</u> ቀድቶ ሰጠኝ።" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ......... ሀረግ ነው።

A. መስተዋድዳዊ

B. ግሳዊ

C. ስማዊ

D. ተውሳከ ግሳዊ



LIVEWORKSHEETS

# አማርኛ ፈተና 8ኛ ክፍል 2017 ዓ.ም

54. "አለሙ ወደ ገበያ ሄዶ እህል ሸመተ።" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ምንድነው?

A. የግስ ገላጭ

B. የስም ገላጭ

C. ስማዊ ሀረግ

D. ግሳዊ ሀረግ

55. "የጸሀይ ብርሃን ለጤንነት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው።" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ምንድነው?

A. የግስ ገላጭ

B. ግሳዊ ሀረግ

C. ስማዊ ሀረግ

D. የስም ገላጭ

56. "ከገበያው በታች ፎቅ ተሰርቷል።" የሚለው አረፍተ ነገር ከየትኛው የአረፍተ ነገር አይነት ይመደባል?

A. ጥያቄያዊ

B. ተገብሯዊ

C. አጋኗዊ

D. ገቢራዊ

57. "ድንቂቱ የሚያምር ቀሚስ ገዛች።" የሚለው ምን አይነት አረፍተ ነገር ነው?

A. ገቢራዊ

B. ትእዛዛዊ

C. ተገብሯዊ

D. አጋኗዊ

58. "ለገበያ ያቀረብሽው አትክልት የተበላሸ ነው እንዴ?" የሚለው አረፍተ ነገር በየትኛው የአጻጻፍ ስልት የቀረበ ነው?

A. ትእዛዛዊ

B. ሀተታዊ

C. ጥያቄያዊ

D. አጋኗዊ

59. "ለታላቅ እህቴ የሀገር ልብስ ገዛሁላት።" የሚለው አረፍተ ነገር ከአገልግሎት አንጻር ከየትኛው የአረፍተ ነገር አይነት ይመደባል?

A. ትእዛዛዊ

B. ተገብሯዊ

C. አጋኗዊ

D. ሀተታዊ

60. "የዚህ ከተማ ወጣቶች ዘፈን ማዳመጥ ይወዳሉ።" የሚለው አረፍተ ነገር ባለቤት ....... ነው።

A. የዚህ ከተማ

B. የዚህ ከተማ ወጣቶች

C. ዘፈን ማዳመጥ

D. ማዳመጥ ይወዳሉ



LIVEWORKSHEETS